

ሕይወትህን ተደሰትባት

በ ዶ/ር ሙሐመድ ቢን አብዱረህማን አል አሪፈ

ትርጉም ሐድያ ሙሐመድ

ህይወትህን ተደሰትባት

ዝግጅት፦ ዶ/ር ሙሐመድ ቢን
አብዱረህማን አል አሪፋ

ትርጉም፦ ሐድያ መሐመድ

ምሥጋና

የመጀመሪያው ምስጋና ለአላህ ነው፤ አሰጀምሮ ላሰጨረሰኝ። ባለቤቴ አህመድ ዋሴ ሁሌም ከጎኔ ነው።

ይህን መፅሐፍ ለሰጠኸኝና እንድተረጉመው ላበረታታኸኝ ወንድም ጀማል በሸር አላህ ኸይር ጀዛህን ይከፈልህ።

አህቴ ሃያት ሸኩርም ለዚህ መፅሐፍ መሳካት ያደረገችው አስተዋፅኦ ቀላል የሚባል አይደለም። ሃዩ ያለመሰልቸት ሰዎችን ለመርዳት የምታደርጊው ጥረት ያስደንቀኛል። አላህ ስኬታማ ህይወት እንዲያጎናፅፍሽ የዘወትር ምኞቴ ነው።

በትየባው የተባበራችሁኝ ሂሩት ኃይሉና መርየም ሙሐመድ አሚን ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ማውጫ

መቅድም	9
መግቢያ	10
አይጠቀሙም	11
ምን እንማራለን?	13
ከሀሎቶች ለምን ያስፈልገናል?	14
ራስህን አሻሽል	17
ለፈሰሰ ውተት አታልቅስ	19
ልዩ ሁን	21
ለርስዎ በጣም ተወዳጅ ሰው ማን ነው?	23
በከሀሎቶች ተደሰት	28
ከድሆች ጋር	31
ከሴቶች ጋር	33
ከልጆች ጋር	36
ከአገልጋዮችና ከሠራተኞች ጋር	39
ከችግሮች ጋር	41
ከእንስሳት ጋር	46
የሰውን ልብ ለማሸነፍ የሚያስችሉ ዘዴዎች	48
ኒያህን አጥራ	50
ትከከለኛውን ጣዕም ተጠቀም	53
ትከከለኛውን ርዕስ ምረጥ	61
በመጀመሪያው ግንኙነትህ ደግ ሁን	66
የመዓዛያ ፀጉር	70
የልቦች ቁልፍ	73
የሰውን ስነልቦናዊ ሁኔታ ከግንዛቤ አስገባ	76
ለሰዎች አስብ	80
ጥሩ ነገር እንደምትመኝላቸው አሳያቸው	88

ስሞችን አስታውስ	90
ጥሩ በሆነ ነገር ላይ ብቻ አስተያየት ስጥ	92
በማያገባህ አትግባ	94
ጣልቃ ገቦችን እንዴት ማስተናገድ ይቻላል?	97
አትተች	99
አንባገነን አትሁን	103
ልምጩን መሀል ላይ ያዘው	108
ስህተትን ማረም ቀላል ነው	113
ሌላው አስተያየት	119
ላመናጨቀህ ሰው በትህትና መልስለት	123
ስህተቱን አሳምነው ምክር ይቀበል ዘንድ	128
አትተቸኝ! የታሪኩ መጨረሻ?	132
ከመተቸትህ በፊት ስህተት መኖሩን አረጋግጥ	139
አስተውለህ ግረፈኝ!	142
ከችግሮች ራቅ!	144
ስህተትህን ተቀበል ግትር አትሁን	149
የስህተቶች ቁልፍ	153
ጥቅሉን ፍታ	158
ራስን መቅጣት	162
መፍትሄ የሌላቸው ችግሮች	166
በሀዘን ራስህን አትግደል	167
አላህ በሰጠህ ነገር ተብቃቃ	170
ተራራ ሁን	174
መጠጥ በመጠጣቱ አትርገመው	177
የምትፈልገው ካልሆነልህ የሆነልህን ፈልግ	178
በሃሳብ ላንስማማ እንችላለን፤ ነገር ግን ወንድማማቾች ነን	180
ማስተዋል ውበት ነው	183
በሞቱትና ባሉት መካከል	190

ምላስህን ጣፋጭ አድርግ	196
ግልፅ ሁን፤ አትከራከር	201
ሰዎች ስለሚያወሩት ነገር አትጨነቅ	203
ፈገግ በል፤ ሁሌም ፈገግ በል	205
ቀይ መስመር	207
ሚስጥር መጠበቅ	210
የሰዎችን ፍላጎት መሟላት	214
በራስህ ላይ ጫና አትፍጠር	217
ድመቷን ማን መታት?	220
ትህትና	225
በድብቅ ሊባዳ ማድረግ	227
ከጉድጓዱ አውጣቸው	232
ሰውን በአለባበሱ አትገምግም	234
ታማኝነት	237
መርሆችህ ላይ ጽና	239
ፈተና	242
ይቅር ባይነት	245
ቸርነት	250
ሰዎችን ከመጉዳት ታቀብ	255
ጠላት አታፍራ	258
ምላስ ንጉስ ነው	259
ምላስህን ጠብቅ	263
ቁልፍ	266
የስሜት ቀሪ ሂሳብ	271
አስማተኛው	273
በሌላ ነገር መርዳት ባትችል በንግግርህ እርዳ	278
ዱዓ	283
መጠገን	291

በሁለቱም ዓይኖችህ ተመልከት	294
የማዳመጥ ጥበብ	297
የውይይት ጥበብ	301
አላግባብ ትችት የሚያቀርቡ ሰዎችን መንገድ ዝጋ!	305
ጠበቅ አታድርጥ	307
ከመጠየቅህ በፊት ስጥ	309
ሁሌ ስኬታማ መሆን አይቻልም	314
ጀግና ሁን አሁኑኑ ጀምር	315

መቅድም

የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጡር ነው። ብቻውን መኖር አይችልም። ቤቱ ውስጥ ከሚስቱና ከልጆቹ፣ ወጣ ሲል ከጎረቤቶቹ፣ መንገድ ላይ ከትራንስፖርት ተጠቃሚዎች፣ በስራ ቦታው ከስራ ባልደረቦቹ፣ እንዲሁም ከዘመዶቹና ከጓደኞቹ ጋር ይገናኛል። ከነዚህ ሁሉ ጋር በጥሩ ሁኔታ መግባባት ከቻለ ፍቅራቸውን ያገኛል። የሰዎችን ፍቅር የሚያገኝ ሰው ደስተኛ ነው። ደስተኛ ህይወትን ይመራል። ጥሩ የመግባባት ችሎታ ከሌለው ግን በተለያዩ መንገዶች ሰዎችን ያስቀይማል። በዚህ የተነሳም ሰዎች ይርቁታል። ይህ ነገር ይረብሸዋል። ሰላሙንና ደስታውን ይነጥቀዋል። ከሰዎች ጋር በጥሩ ሁኔታ መግባባት የተወሰኑ ከህሎቶችን ይጠይቃል። አንዳንዶች በተፈጥሯቸው እነዚህን ከህሎቶች የያዙ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ከህሎቶቹን መማር ይኖርባቸዋል። ያለኝን ባህሪ መቀየር አልችልም አትበል። "ባህሪን መቀየር ልብስን የመቀየር ያህል ቀላል ነው" ይላሉ የዚህ መፅሐፍ አዘጋጅ። የሚያስፈልገው ፅናትና ቁርጠኝነት ብቻ ነው። ይህን መፅሐፍ ኢስተምተእ ቢሃያቲክ በሚል ርዕስ ያዘጋጁት ዶ/ር ሙሐመድ ቢን አብዱረህማን አልዓሪፈ ናቸው። ሳሊም ቤግ ኢንጆይ ዩር ላይፍ ብለው ወደ እንግሊዝኛ መልሰውታል። እኔም ህይወትህን ተደሰትባት በሚል ርዕስ በአማርኛ ተርጉሜዋለሁ። ድንቅ መፅሐፍ ነው። እውነተኛ ደስታን ይሰጣል። አንብበው የደስታው ተካፋይ ቢሆኑስ?

ሐድያ ሙሐመድ

መግቢያ

ምስጋና ለአላህ፤ የአላህ ሶላትና ሰላም በመጨረሻው ነብይ ላይ ይሁን። የአስራ ሰባት ዓመት ልጅ እያለሁ ነው "ህው ቱ ዊን ፍሬንድስ ኤንድ ኢንፍሉዌንስ ፒፕል" የሚለውን የዴል ካርኒጌን መጽሐፍ ያየሁት። በጣም ጥሩ መጽሐፍ ሆኖ ስላገኘሁት ለበርካታ ጊዜያት አነበብኩት። ደራሲው መጽሐፉን በወር አንዴ ማንበብ እንደሚጠቅም ይመክራል። በተደጋጋሚ እያነበብኩ መርሆዎቹን ከሰዎች ጋር ባለኝ ግንኙነት ተግባራዊ ማድረግ ጀመርኩ። አስገራሚ ውጤትም አገኘሁ። ካርኒጌ መርሆችን ያስቀምጥና እንደነ ሩዝቬልት፣ ሊንከን፣ ጀሴፍ ወዘተ... ካሉ ታዋቂ ሰዎች ጋር የተገናኙ በርካታ ምሳሌዎችን ያመጣል። ሳስበው የደራሲው ብቸኛ ግብ ዓለማዊ ደስታን ማግኘት ነው። የእስልምናን ህግና ደንብ ቢያውቅና ይህን አስደናቂ ከሀሎቱን ወደ ኢባዳ ቀይሮ ከአላህ ጋር ቢቀርብበት እንዴት ጥሩ ነበር? በርግጠኝነት ዓለማዊና ዘላለማዊ ደስታን ይጎናጸፍ ነበር። በተለይ ደግሞ ካርንጌ ራሱን ማጥፋቱን ስሰማ መጽሐፉ ምንም እንኳ ጠቃሚ ቢሆንም ለሱ እንዳልጠቀመው አረጋገጥኩ። ከዚያም ወደራሳችን ተመልሼ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ)፣ የባልደረቦቻቸውንና የዚህን ኡማ ታላላቅ ሰዎች ታሪክ ስመለከት በቂ ትምህርት የሚሰጥ ሆኖ አገኘሁት። እናም ይህን መጽሐፍ መፃፍ ጀመርኩ። ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ምን መምሰል አለበት?

ይህ መጽሐፍ የጥቂት ወራት ወይም የጥቂት አመታት ጥንቅር ሳይሆን የሃያ ዓመት ጥልቅ ጥናት ውጤት ነው። አላህ /ሱ.ወ/ ጥቂቶቹ በሚሊዮኖች ኮፒ እየታተሙ ያሉ ከሃያ በላይ መጽሐፍት የማዘጋጀት ችሎታ ቢያድለኝም ከሁሉም በላጩ፣ ተወዳጁና ልዩው መጽሐፍ ይሄኛው ነው ብዬ አምናለሁ። ይህን መፅሐፍ በደሜ በተሞላ ብዕር ነው የጻፍኩት። ይህ መፅሐፍ ላይ ነፍሴን አፍስሼበታለሁ። ትዝታዬን ጨምቄበታለሁ። የዚህ መፅሐፍ ቃላት የወጡት ከልቤ ጥልቅ ከፍል ነው። ስለሆነም የአንባቢያን ልብ ውስጥ ጠልቀው ይገባሉ የሚል ተስፋ አለኝ። እናም ሰዎች እነዚህን አስተምህሮቶች ተግባራዊ ሲያደርጉ፣ በጥበባቸው ላይ መሻሻል ሲያመጡና በህይወታቸው መደሰት ሲጀምሩ ባይ አረካለሁ። አላህም ለሱ ሰል ነውና ይህን ሁሉ ጥረት ያደረግኩት ምንዳዬን እንዲሰጠኝና ሰዎችንም ከዚህ መፅሐፍ ተጠቃሚ እንዲያደርግልኝ አለምነዋለሁ።

ሁሌም ጥሩ ነገር እንዲገጥማችሁ የሚመኝላችሁና ዱዓ የሚያደርግላችሁ ወንድማችሁ፡-

ዶ/ር ሙሐመድ ቢን አብዱረህማን አልዓሪፈ



አይጠቀሙም

በአንድ ወቅት ሞባይል ስልኬ ላይ አንድ የጽሑፍ መልዕክት አገኘሁ። ጥያቄ ነው። "ውድ ሼህ ሆይ! ራስን ማጥፋት የሚያስከትለው ቅጣት ምንድን ነው?" ይላል። አንድ ወጣት ነው የላከው። ደወልኩለትና "ይቅርታ ጥያቄህ አልገባኝም እባክህን ድገምልኝ?" አልኩት። እሱም "ጥያቄው ግልጽ ነው። ራስን ማጥፋት የሚያስከትለው ቅጣት ምንድን ነው?" አለኝ በተሰበረ ድምጽ። እንግዳ የሆነ መልስ ሰጥቼ ላስደንቀው ፈለግኩና "ራስን ማጥፋት ይቻላል" አልኩት። "ምን?!" አለና ጮኸ።

"በተገቢው መንገድ ትፈፅመው ዘንድ ግን ለምን አንወያይበትም?" አልኩት። መልስ አልሰጠኝም።

"ለምን ራስህን ማጥፋት ፈለግክ?" አልኩት።

"ስራ ማግኘት አልቻልኩም። ሰዎች አይወዱኝም። በአርግጥ እኔ የአቀራረብ ችግር አለብኝ ... " በማለት ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል ያደረገው ጥረት እንዳልተሳካለትና ከሀሎቱን መጠቀም እንዳልቻለ የሚጠቁም ረጂም ታሪክ ይዘረዝርልኝ ጀመር። ይህ የብዙ ሰዎች ችግር ነው። ለምንድን ነው ብዙዎቻችን የቢታችነት ስሜት የሚሰማን? እነሱ ከደረሱበት መድረስ እንደማንችል በማሰብ ተራራ ጫፍ ላይ ያሉ ሰዎችን ለምን እንመለከታለን?

ተራራ ለመውጣት ልቡ ያልደፈረ
ይቀራል ጉድጓድ ውስጥ እንደተቀበረ።

ከዚህ መጽሐፍ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ መጽሐፍት ተጠቃሚ የማይሆን ሰው ማን እንደሆነ ማወቅ ትፈልጋላችሁ? ለስሀተቶቹ እጅ የሰጠና በውስጡ ከሀሎቱ የረካ አድለ ቢስ ሰው። "ይህ ተፈጥሮዬ ነው። ይሄን መቀየር አልችልም። እንደዚህ መሆኔን ሁሉም ሰው ያውቃል። እኔ እንደ ኻሊድ ጥሩ ተናጋሪ መሆን አልችልም። ወይም እንደ አህመድ ተግባቢ መሆን አልችልም። እኔ እንደ ዚያድ ሰው ሁሉ ሊወደኝ አይችልም። ይህ ሊሆን አይችልም። ያ ሊሆን አይችልም።" በአንድ ወቅት ከአንድ አዛውንት ጋር ስብሰባ ላይ ተገናኘን። አብዛኞቹ ታዳሚዎች ጥሩ ጥበብና ችሎታ ያላቸው ሰዎች ናቸው። ሽማግሌው ከጎናቸው ካለው ሰው ጋር በማውራት ተጠምደዋል። ስብሰባው

ላይ የተጋበዙት የረጂም እድሜ ባለፀጋ በመሆናቸው ነው። ንግግር አደረግኩ። በንግግሬም የሸይኽ አብዱል አዚዝ ቢን ባዝን ብይን ጠቅሼ ነበር። ጨርሼ ስቀመጥ ሽማግሌው በኩራት "እኔና ኢብኑ ባዝ ጓደኛሞች ነበርን። ከአርባ ዓመት በፊት ከሸህ ሙሐመድ ኢብን ኢብራሂም ላይ አብረን ተምረናል" አሉ። ይሆን መረጃ ለኔ መንገር እንደፈለጉ ስላወቅኩ ዘወር አልኩ። በህይወታቸው የአንድ ስኬታማ ሰው ጓደኛ ስለነበሩ በጣም ደስተኛ ናቸው። ለራሴ እንዲህ አልኩ፡- "ምስኪን ለምን እርስዎም እንደ ኢብኑ ባዝ ስኬታማ መሆን አልቻሉም? የስኬትን መንገድ አግኝተው ከነበር ለምን በዚያ መንገድ አልቀጠሉም? ኢብን ባዝ የሞቱ አለት ሰዎች በየሚንበሩ፣ በየተቋሙ፣ በየማህበሩ፣ በየመድረኩ አልቅሰውላቸዋል። በርካታ ህዝብ ነው በሳቸው ሞት ያዘነው። እርስዎ ሲሞቱ ግን በርህራሄና በባህል ካልሆነ በስተቀር አንድ ጠብታ እንባ የሚያፈስ ሰው የለም።" ብዙዎቻችን ስለ ስኬታማ ሰዎች ስንሰማ "እከሌ አብሮ አደጌ ነው።" "እከሌ ጋር አብረን ተምረናል።" "እከሌን በደንብ አውቀዋለሁ" ወዘተ ስንል እንደመጣለን። ይህ ግን ምንም አያኮራም። የሚያኮራው እነሱ የደረሱበት ደረጃ ላይ መድረስ ነው። ጠንክር በልና ከዛሬ ጀምሮ ያሉህን ችሎታዎች በሙሉ ለመጠቀም ቁርጠኛ ሁን። ፊትህ ላይ ያለውን መኮሳተር በፈገግታ፣ ድብርትን በሀሴት፣ ስስትን በቸርነት፣ ቁጣን በታጋሽነት፣ የችግር ቀናትን በደስታ ቀናት ተካ። እምነትህን ወደ መሳሪያ ቀይረው። ከዚያም ስኬታማ ትሆናለህ።

ህይወትህን ተደሰትባት። ምክንያቱም ለሜንቀት ጊዜ የለህም። ይህን እንዴት ማድረግ ይቻላል? ለዚህ ነው ይህን መጽሐፍ ያዘጋጀሁት። እስከመጨረሻው ከኔ ጋር ቆይ። በአላህ ፈቃድ።

ከእኛ ጋር ትቆያለህ_

የራስህን ጥበባት የማሳደግ ውሳኔና ጽናት ካለህ። ከብቃትህና ከችሎታህ የመጠቀም ፍላጎት ካለህ።



ምን እንማራለን?

ሰዎች ለሚያጋጥሟቸው ከስተቶች የተለያዩ ስሜቶችን ያንፀባርቃሉ። ሀብት ሲያገኙ፣ የስራ ልድነት ሲሰጣቸው፣ ከበሽታቸው ሲፈወሱ ይደሰታሉ። ዓለም ፈገግ ስትልላቸውና ምኞታቸው ሲሳካ ይስቃሉ። ሀመም ሲነካቸው፣ ውድቀት ሲያጋጥማቸውና ሲደክዩ ያዝናሉ። ይህ መሆኑን ካወቅን እንዴት ደስታችን ከሀዘናችን የሚልቅና ቋሚ ማድረግ እንደምንችል እንመልከት። አዎ፣ ዓለም ጣፋጭም መራራም ናት። በዚህ እንስማማለን። ነገር ግን ቢደረሱበን ችግርና መከራ ላይ ብቻ በማተኮር ለምን ለበርካታ ቀናት እናዝናለን? በአንድ ነገር ላይ ለማዘን አንድ ሰዓት በቂው ሆኖ ሳለ ለበርካታ ሰዓታት ይታዘናል። ለምን?

በእርግጥ ሀዘንና ሞንቶት ልባችን ውስጥ የሚገቡት ፈቃድ ሳይጠይቁ መሆኑን አውቃለሁ። ነገር ግን ለእያንዳንዱ የተከፈተ የሀዘን መግቢያ በር ከአንድ ሺ በላይ የመቆለፊያ ዘዴዎች አሉት። ቀጥለን የምናብራራው እነሱን ነው። ትኩረታችሁን ወደ አንድ ሌላ ጉዳይ እንድወስድ ፍቀዱልኝ። በብዙ ሰው ዘንድ የሚወደዱ ብዙ ሰዎችን አይተናል። ሰዎች ሁሉ ሊያገኝዋቸውና ሊጎበኝዋቸው ይፈልጋሉ። ነገር ግን እንደነሱ ለመሆን አይመኙም። ሁሌ በነዚህ ሰዎች ባህሪ ይደነቃሉ። ራሳቸው ተደናቂ ለመሆን ግን አይሞክሩም። ቀጥለን እንዴት አስደናቂ መሆን እንደምንችል እንይ። የአንትህ ልጅ በስብሰባ ላይ ንግግር ሲያደርግ ለምንድን ነው ሰው ሁሉ ተመስጦ የሚያዳምጠው? ሰዎች በአነጋገር ለዛው ለምን ይደመማሉ? አንተ ስትናገር ፊታቸውን የሚያዞሩትና እርስ በርስ የሚንሾካሾኩት ለምንድን ነው? ለምን? አንተ ከሱ የተሻለ እውቀት፣ ችሎታና ደረጃ ሊኖርህ ይችላል። ታዲያ እሱ እንዴት ትኩረት ሊያገኝ ቻለ? አንተ ለምን አልቻልከም? ለምንድን ነው አንድ አባት ከስራ ወደ ቤት ሲገባ ልጆቹ ዘለው የሚያቅፉትና በሚሄድበት ሁሉ ተከትለውት ለመሄድ የሚፈልጉት? ሌላኛውስ ልጆቹን አብረን እንሂድ ብሎ ሲለምናቸው ከሱ ጋር ላለመሄድ አስሩን ምክንያት የሚደረድሩት ለምንድን ነው? ሁለቱም አባቶች አይደሉ? ለምን ልዩነት ተፈጠረ?

እዚህ ላይ ህይወትን እንዴት እንደምንደሰትባት እንማራለን። ሰዎችን ለመሳብ የሚያስችሉህን የተለያዩ ዘዴዎች እወቅ። በጎ ተጽእኖ አሳድርባቸው። ከስህተቶቻቸው ጋር ተላመድ። መጥፎ ባህሪ ካላቸው ሰዎች ጋር ተግባባ። ብዙ ብዙ ነገሮችን አድርግ። ስለዚህ እንኳን ደህና መጣህ!

አንድ ቃል...

ስኬት ሰዎች የሚወዱትን ነገር ማወቅ አይደለም። ፍቅራቸውን ለማግኘት የሚያስችሉ ጥበቦችን ማግኘትና እነዚያን ተግባራዊ ማድረግ እንጂ።



ከሀሎዶች ለምን ያስፈልጉናል?

በአንድ ወቅት ወደ አንድ የገጠር ከተማ ዳዕዋ ለማድረግ ሄድኩ። ከዳዕዋው በኋላ አንድ አስተማሪ መጣና "ለጥቂት ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ እንደምታደርግልን ተስፋ አደርጋለሁ" አለኝ። "ትምህርት ቤቶቹ በመንግስት የሚደገፉ ናቸው። የነፃ ትምህርት አይሰጡም እንዴ?" አልኩት።

"ይደገፋሉ። የዩንቨርሲቲ ወጪያቸውን ለመሸፈን ነው" አለኝ። "ዩንቨርሲቲዎችም ቢሆኑ ወጪያቸው በመንግስት ነው የሚሸፈነው። እንደውም ለተማሪዎች ስጦታዎችን ሳይቀር ይሰጣሉ" አልኩት። "ፍቀድልኝና ላስረዳህ" አለኝ።

"እሺ" አልኩት።

"ተማሪዎቻችን በጣም ጎበዞች ናቸው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ከ99% ባላነሰ ነጥብ ነው። ጭንቅላታቸው ለኡማው ቢከፋፈል ይበቃል። ነገር ግን አንድ ተማሪ ውጤት አምጥቶ ህክምና፣ ምህንድስና፣ ኢስላማዊ ህግ፣ ኮምፒዩተር ሳይንስ... ወዘተ ለማጥናት ወደ ሌላ ከተማ ሊሄድ ሲነሳ አባቱ እስካሁን የተማርከው ይበቃሃል። ከአንግዲህ አርፈህ ተቀመጥና የከብት እረኛ ሁን በማለት "ዩንቨርሲቲ ከመግባት ይከለክለዋል" አለኝ። "የከብት እረኛ?!" በድንጋጤ ጮህኩ።

"አዎ የከብት እረኛ!" አለ።

እናም ምስኪኑ ልጅ እዚሁ ይቀርና ከብት እረኛ ይሆናል። ችሎታው ሁሉ ይባክናል። በከብት እረኝነት እድሜውን ይጨርሳል። አባቱ በሱ ላይ የፈፀመውን ተግባር እሱም በልጆቹ ላይ ይፈፅማል። እናም ልጆቹ በሙሉ የከብት እረኛ ሆነው ይቀራሉ።

"ታዲያ መፍትሄው ምንድን ነው?" አልኩት።

"መፍትሄው አባት እኛ በምንሰጠው ጥቂት መቶ ሪያሎች ከብት ጠባቂ እንዲቀጥርና ልጅ ሙሉ ችሎታውንና ጥበቡን እንዲጠቀም እንዲፈቅድለት ማሳመን ነው። ልጁም እስኪመረቅ ድረስ በገንዘብ እናግዘዋለን። መምህሩ ጭንቅላቱን ወደ

መሬት በመድፋት "ይሀን የመሰለ ሜንትላቶች መላከናቸው በጣም ያሳገሩናል። ልንጠቀማቸው እየቻልን" አለ።

የተናገረውን ነገር ሳስላስለው ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ የምንችለው ያሉንን ችሎታዎች ስንጠቀምና የሌሉንን መፈለግ ስንችል ብቻ እንደሆነ ተረዳሁ።

እስቲ ስኬታማ የሆኑ ሰዎችን ተመልከቱ። ስኬታቸው በትምህርት፣ በዳዕዋ፣ በንግድ፣ በሀገምና፣ በምህንድስና፣ ሰዎች ላይ ተጽእኖ በማሳደር አለያም በቤተሰባዊ ህይወት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ከልጆቹ ጋር ስኬታማ የሆነ አባት፣ ወይም ከባሏ ጋር ስኬታማ የሆኑች ሚስት ወይም በማህበራዊ ህይወታቸው ስኬታማ የሆኑ ሰዎችን ለምሳሌ ከጎረቤቶቹ፣ ከጓደኞቹ ጋር ስኬታማ የሆነ ሰው ሊሆን ይችላል። አሰቦበትም ሆነ ሳያስበው ከሰዎች ጋር የመግባባት ከሀሎትን ተግባራዊ ሳያደርግ ስኬታማ የሆነ አንድ ሰው አታገኙም። አንዳንድ ሰዎች ሳያስቡት እነዚህን ከሀሎቶች ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሌሎቹ ደግሞ ስኬታማ ለመሆን እነዚህን ጥበባት መማር ይኖርባቸዋል። ጥበብን ተምረው ያገኙ ስኬታማ ሰዎች እንዴት ስኬትን እንደተጎናፀፉ ለማወቅና የነሱን የስኬት ጎዳና መከተል እንችላለን ወይስ አንችልም የሚለውን ለማረጋገጥ ህይወታቸውን ማጥናትና ዘዴዎቻቸውን መከተል ግድ ይለናል።

በቅርቡ አንድ ዓለም አቀፍ ሀብታም ከአንድ የሚዲያ ተቋም ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ አድምጬ ነበር። ሸይኽ ሱለይማን አልራጂሂ ይባላል። ቢሊየነር ነው። በባህሪውም ሆነ በአስተሳሰቡ እንደተራራ የገዘፈ ሰው ሆኖ ነው ያገኘሁት። በርካታ ሪል ስቴቶች አሉት። በመቶዎች

የሚቆጠሩ መስጊዶችን ሰርቷል። በሺዎች የሚቆጠሩ ወላጅ አልባ ህፃናትን ይረዳል። እጅግ በጣም ስኬታማ ሰው ነው። ከሃምሳ አመት በፊት ግን ከአለት ጉርሱ የሚዘል ገንዘብ አልነበረውም። አንዳንዴ ያንንም ያጣ ነበር። ራሱን ለመመገብ የሰው ቤት ያፀዳ ነበር። በምሽት ደግሞ ሱቆችና ሃዋላ ቤቶች ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራል። በአንድ ወቅት ከተራራ ስር እንደነበረና ከተራራው ጫፍ ላይ ለመድረስ ብዙ መልፋቱን ሲናገር ሰማሁት። ይህ ሰው ያለውን ችሎታና ጥበብ ካሰብኩ በኋላ ብዙዎቻችን እንደሱ የመሆን አቅም እንዳለን ተረዳሁ። አንድ ሰው እነዚህን ከሀሎቶች ከተማረ፣ ተግባራዊ ካደረጋቸውና ፅናት ካለው እንደዚህ ሰው መሆን ይችላል።

እነዚህን ከሀሎቶች ለመፈለግ የሚያስገድደን ሌላው ምክንያት አንዳንዶቻችን በውስጣችን የተደበቁና ያላወቅናቸው፣ እነሱን ለማውጣት እንድንችልም ማንም ያላገዘን የተወሰኑ ችሎታዎች ሊኖሩን ይችላሉ። ለምሳሌ የንግግር ከሀሎት፣ የንግድ ከሀሎት፣ ወይም የጠቅላላ አውቀት ከሀሎት። አንድ ሰው እነዚህን ከሀሎቶች በራሱ ሊያገኛቸው ይችላል። አለያም በመምህር፣ በጓደኛ ወይም በጥሩ ወንድም አገዛ።

ካልሆነ ግን በሰውዬው ውሳጥ ተቀብረው ይቀራሉ። ይህ ሲሆን ሀላችንም አንድ ጥሩ መሪ፣ አስተማሪ፣ ምሁር ወይም ስኬታማ ባል ወይም ጥሩ አባት አጣን ማለት ነው። ቀጥሎ ጥቂት ከህሎቶች እንጠቅሳለን። ካለህ ልናሲታውሰህ ከሌለህ ደግሞ ልናሰለጥንህ። ተከተለን!

አንድ ትምህርት...

ተራራውን ውጣ። የተራራውን ጫፍ እንጂ በዙሪያህ ያሉትን ድንጋዮች አትመልከት። የት መርገጥ እንዳለብህ ብቻ አስተውል። አትዝለል። ሊያንሸራትትህ ይችላልና።